የጂማው ሡልጣን ዳግማዊ አባጂፋር ፣ ለምኒልክ እንገብራለሁ ካሉ በኋላ ዛንዚባር ካሉ አረቦች ጋር በመላላክ ወዳጅነት ፈጥረው ነበር ። አባጅፋር የአባታቸውን የጐሞልን ዙፋን የወረሱት በ1870 ዓ. ም. ነው ። በግዛቱ ውስጥ መነጋገሪያው ቋንቋ አረብኛ እንዲሆንና የአረብኛ ትምህርት እንዲሰጥ ታወጀ ነበር ። በኢትዮጵያ ያለው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የተሻለ ኑሮ ለመመሥረት ወይም ለንግድ ከሸዋ ፣ ከወሎ ፣ ከጐጃም ፣ ከጐንደር ወደ ጂማ የሚገባውን ሰው ሁሉ እያስያዙ በግድ በእስልምና ሃይማኖት እንዲገቡ ያደርጉ ጀመር ። ይህን የሰሙት ንጉሥ ምኒልክ “ . . . . አገሩን የአረብ አገር ማድረግህ እንደ ሆነ ቁርጡን ንገረኝና ውላችን ይፍረስ . . . .” ብለው ላኩባቸው ። አባጅፋርም መልስ ሳይሰጡ ዝም አሉ ። ምኒልክም በትግስት ጠበቁ ።

ንጉሥ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ከተባሉ በኋላ በ1882 ዓ. ም. ሕዳር 9 ቀን አባጅፋር ግብር ለመገበር ወደ ምኒልክ ዘንድ መጡ ። አጤ ምኒልክም “. . . .ካገርህ የገባውን ክርስቲያን ሁሉ ሰብስበህ አምጣ . . . .” ብለው አባጂፋርን በወህኒ አዛዥ ወልደጻዲቅ እጅ አስጠበቋቸው ። አባጂፋርም ባገራቸው ውስጥ ያለውን ክርስቲያን ሁሉ ለቀቁ ። ከዚህ በኋላ አገራቸውን መልሰው ሰጥተው ሾመው ሸልመው ሰደዷዋቸው ።

አባጂፋር በአባታቸው ሥልጣን ሥርና ራሳቸውን ችለው ከ1861 ዓ. ም. ጀምሮ እስከ 1934 ዓ. ም. ድረስ ጂማን የገዙ ባላባትናቸው ። አባጅፋር ለምኒልክ ገብረው የምኒልክ ወዳጅ ሆነዋል ። ጂማንም ቢሆን በንግድ የታወቀች አገር አድርገዋታል ። በተለይ በባርያ ንግድ አገሪቱ እውቅ በመሆንዋ ምኒልክ ይህን የባርያ ንግድ እንዲተዉ በ1902 ዓ. ም. የካቲት 8 ቀን በተፃፈ ደብዳቤ አስጠነቀቋቸው ።

ይድረስ ካባ ጅፋር

ይህንን የደንብ ወረቀት ጽፈንልሃል ።

ከጃንጀሮ ወዳንተ አገር የመጣውን ጋላ እንግዲህ ከጂ ከገባ ልኝ ብለህ ጭቡ አድርገህ ባርያዬ ነህና አንተንም ልበድልህ ፤ልጅህንም አምጣና እንደከብት ልሽጠው ፤ ልለውጠው አትበል ። ይህን ያህል ዘመን አባቶቻቸው ከአባቶችህ ፤ ልጆቹ ካንተ ጋር አብረው ኑረው ባርያ ሊባሉ አይገባም ። ባደባባይም ባርያዬ ነው እያልክ አትሟገት ። የሰው ባርያ የለውም ። ሁላችንም የእግዚአብሔር ባርያዎች ነን ። እግዚአብሔር መርጦ ፤ ከሰው አልቆ ሲያስገዛ ጊዜ በሰው መጨከን አይገባም ። ለሰው ቢያዝኑ ዕድሜ ይሰጣል ።





አባጂፋር

